# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮንስትራክሽን ቢሮ

## የፕሮጀክት ኦዲት መመሪያ ቁጥር

4/2010

መጋቢት 2010 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## መግቢያ

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ እጅግ ግዙፍ ካፒታል እና የሰው ሀብት የሚያንቀሳቅስ ለአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እድገት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ዘርፍ ነው፡፡ ሴክተሩ ከሚያንቀሳቅሰው ካፒታል አኳያ በአግባቡ ካልተመራ ሊያስከትለው የሚችለው የሀብት ብክነት የዚያኑ ልክ ከፍተኛ ነው፡፡

በከተማችን ያለው ነባራዊ ሁኔታ ሲታይም በቅርብ እዜያት ከፍተኛ እምርታ እያሳዩ ካሉት የኢኮኖሚ ዘርፎች ዋነኛው የኮንስትራክሽን ዘርፍ ቢሆንም ፕሮጀክቶች ከቅድመ ግንባታ እስከ ፍፃሜያቸው ድረስ አግባብነት ያላቸውን ሕጎችና መስፈርቶች ተከትለው እየተፈፀሙ መሆናቸውን ቴክኒካል ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርግ የተለየ የኦዲት መዋቅር ባለመኖሩ ፤ ሴክተሩ ለዘርፈ ብዙ የጥራት መጓደሎችና ብክነቶች እየተጋለጠ የሚጠበቅበትን ውጤት ከማስመዝገብ አንፃር ክፍተቶች ታይተውበታል፡፡

በዚህ መሰረት በሴክተሩ ውሰጥ በቅድመ ግንባታ፣ በድህረ ግንባታ ወቅት የኮንስትራክሽን ፕሮጅክቶች ከዲዛይን ጥራት፣ ከጨረታ አወጣጥ፣ የክፍያ ስርአት፣ ተቀባይነት ካለው የኮንስትራክሽን ኮንትራት አስተዳደር እና ፕሮጅክቶችን በተያዘላቸው ጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ከማጠናቀቅ አኳያ ተገቢውን የክትትልና ቁጥጥር አሰራር ሰርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ ፤

ግንባታዎች ከዘርፉ የሚጠበቀውን የሙያ ስነ ምግባር በተከተለ አገባብ መከናወናቸውን፣ የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀው መፈጸማቸውን፣ የወጣው ወጪ እና የተከናወነው ግንባታ ተመጣጣኝ መሆኑን አግባብነት ባለው አካል ኦዲት ሊደረግበት የሚችልበተን ሰርዐት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የኮንስትራክሽን ኮንትራት ሕጎች፣ደንቦችና መመሪዎች፣ ደረጃዎችና ስታንዳርዶች እንዲተገበሩና አፈጻጸማቸውን ክትትል ለማድረግ የሚያስችል አሰራር ስርዓት መዘርጋት ተገቢ በመሆኑ፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮንስትራክሽን ቢሮ በአዋጅ ቁጥር የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 15/2001 አንቀጽ 9 ንኡስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ "የፕሮጀክት ኦዲት መመሪያ ቁጥር" 4/2010 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

   2.1 **"ኮንስትራክሽን"** ማለት ከመሬት በታችና በላይ የሚከናወኑ ህንጻን እና ሌሎች የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን ጨምሮ በቋሚ ንብረቶች ላይ የዕቃዎች እና አገልግሎቶች ጥምር የሆነ የልማት፣ የማስፋፋት፣ የመገጣጠም፣ የጥገና፣ የዕድሳት፣ የማሻሻል፣ የቁፋሮ፣ የማወላለቅ እና የማፍረስ ሥራዎችን የሚያካትት ተግባር ነው።

   2.2"**ሥራ ተቋራጭ**" ማለት አግባብነት ባላቸው የአገሪቷ ሕጎች መሰረት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወይም በክልሎችና በሁለቱም ከተማ አስተዳደሮች ተመዝግቦና የስራ ፈቃድ አውጥቶ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ሥራ የሚሰራ /የሚያካሂድ/ ሰው ወይም ድርጅት ነው።

   2.3**"ክዋኔ ኦዲት"** ማለት ፕሮጀክቶች በዲዛይን በጨረታ እና በግንባታ ያለው ሂደት ህግን፤መመርያንና አሰራርን መሰረት ተደርጎ ስለመፈጸማቸው መመርመር

   2.4**"ፋይናንሻል ኦዲት"** ማለት በውለታው ላይ በተቀመጠው ዋጋ መሰረት ፕሮጀክቶች ስለመፈፀማቸው ኦዲት የማድረግ ሂደት ነው

   2.5"በኮንስትራክሽን ዘርፉ የሚስተዋሉ ቅሬታዎችን መፍታት" ማለት ከደንበኞችና ከባለድርሻ አካላት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ተቀብሎ አስፈላጊውን ህጋዊና ቴክኒካዊ ምላሽ መስጠት

   2.6**"ፕሮጀክት ኦዲት"** ማለት አንድ የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ከአዋጭነት ጥናት፤ የዲዛይን ስራ፤ የጨረታ ሰነድ ዝግጅትና አፈጻጸሙ ጀምሮ ግንባታው እስከ ተጠናቀቀበት ድረስ ያለው አካሄድ የኮንስትራክሽን ሕጎች፣ ኮዶችና ስታንዳርዶች ተከትለው ስለመሄዳቸው እና ጥራታቸውን የጠበቁ ግብዓቶችን ስለመጠቀማቸው ኦዲት የሚያደርግ ክፍል ነው።

2.7"**አማካሪ**" ማለት የንድፍ ባለሙያዎችና አማካሪዎች ምዝገባ መመሪያ ቁጥር 22/2005 የተቀመጡ መስፈርቶችን አሟልቶ በቢሮው ወይም በተገቢው አካል በአማካሪነት የተመዘገበ ማንኛውም ሰው/ ድርጅት ነው፣

2.8"**የምህንድስና ባለሙያ**" ማለት በኮንስትራክሽን ወይም በዲዛንይን ስራ ከሚመለከታቸው አካል ተገቢ የሙያ ፍቃድ እና ደረጃ ተሰጥቶት በግንባታ ስራ ላይ የተሰማራ ባለሙያ ነው።

2.9"**የመንግስት ግንባታ ፕሮጀክት**" ማለት መንግስት በጀት መድቦ በባለቤትነት የሚያስገነባቸው ወይም በህዝብና በመንግስት የጋራ ተሳትፎ የሚካሄዱ የግንባታ ፕሮጀክቶች ናቸው።

2.10 "**ኦዲተር**" ማለት ፕሮጀክቶች ከቅድመ ግንባታ ሂደታቸው ጀምሮ በግንባታ የነበረውን ሂደት የህንፃና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ህጎች፤ የኮንስትራክሽን ኮዶችና ስታንዳርዶች መሰረት የተከናወኑ መሆናቸውን የሚፈትሽ አካል ነው።

2.11 "**ፕሮጀክት**" ማለት አንድን ውጤት ወይም አገልግሎት ለማግኘት እውቀት፣ ሙያ፣ መሳርያዎችና ቴክኒኮች እንደ ግብአት በመጠቀም ለተወሰነ ጊዜ የሚፈፀም ማንኛውም የኮንስትራክሽን ስራ ነው።

2.12 "**ህንፃ አዋጅ**" ማለት የፌደራል ህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ነው ፤

2.13 "**ህንፃ ደንብ፡-** ማለት የፌደራል ህንፃ አዋጅ ቁጥር 624/2001 ተከትሎ የወጣ ደንብ ቁጥር 243/2003 ማለት ነው።

2.14 "**የህንፃ መመሪያ**"፡- ማለት የፌደራል ህንፃ ደንብ ቅጥር 243/2003 ተከትሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 05/2003 ማለት ነው

2.15 "**ቢሮ**" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኮንስትራክሽን ቢሮ ነው፣

2.16 "**ዋና የስራ ሂደት**" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮንስትራክሽን ቢሮ ስር ያለው የፕሮጀክት ኦዲት ዋና የስራ ሂደት ማለት ነው።

2.17 "**የስራ ሂደት አስተባባሪ**" ማለት በስራ ሂደት አስተባባሪነት ማዕርግ የተመደበ የፕሮጀክት ኦዲት ዋና የስራ ሂደት አስተባባሪ ሆኖ ተጠሪነቱ ለቢሮ ኃላፊ የሆነ አካል ነው።

2.18 "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ማንኛውም አካል ማለት ነው።

2.19 በወንድ ፆታ የተገለፀው ለሴት ፆታም ተፈፃሚ ይሆናል።

2.20 "**ሚኒስተር**" ማለት የፌደራል ኮንስትራክሽን ሚኒስተር ማለት ነው

2.21 **"ባለድርሻ አካላት"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፤ ፋይናስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ፤የአከባቢ ጥበቃ ባለስልጣን፤ፍትህ ቢሮ፤ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ቢሮ፤ የኮንስትራክሽን ሚኒስተር፤የኮሚንኬሽን ጉዳዮች ቢሮ ናቸው

2.22 **"የስራ ሂደቱ ተገልጋዮች"** ማለት ስራ ተቋራጮች፤ አማካሪዎች፤ የግንባታ ባለቤት መስሪያ ቤቶች፤ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች፤ የከተማው ነዋሪዎች፤ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፤ የሙያ ማህበራት ናቸው

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

3.1 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ሆኖ በመንግስት በጀት በሚገነቡ ፕሮጀክቶች፣

3.2 በፌደራልና በአዲስ አበባ አስተዳደር መንግስታት በጋራ በሚገነቡ ፕሮጀክቶች፣

3.3 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ ሁሉም ክፍለ ከተማዎች በጀት በሚገነቡ ፕሮጀክቶች

3.4. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ ሁሉም ወረዳዎች በጀት እና በህዝብ ተሳትፎ የሚገነቡ ፕሮጀክቶች

## 4. የፕሮጀክት ኦዲት መርሆዎች

1) ፕሮጀክቶች በሕጋዊነትና ግልፅነት መርህ መሰረት እንዲገቡ በማድረግ ፤የሕዝብና ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ እንዲረጋገጥባቸው ማስቻል፤

2) በኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች የሚሳተፉ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ስራዎቻቸውን የተጠያቂነት መርህ በተከተለ አግባብ መፈፀማቸውን ማረጋገጥ፤

3) ለኮንስትራክሽን ፕሮጀክት በሚውሉ ሀብቶች ( ገንዘብ፤ጉልበት፤እውቀት እና ቁሳቁስ )አስተዳደር ላይ ተገቢ ስራ፣ ውጤት፤ አገልግሎት እና ዋጋ ከማግኘት አኳያ ውጤታማነት እንዲረጋገጥ ማስቻል።

4) የኮንስትራክሽን ስራ ለውጥ በተፈለገበት ፕሮጀክት አሰሪው ለሚያወጣው ተጨማሪ ካፒታል /ገንዘብ/ የሚመጥን ውጤት እና አገልግሎት እያገኘ መሆኑን ማረጋገጥ።

5) በፕሮጀክት ወጪ ጊዜ ጥራትና ግብዓቶች ላይ ነፃ ሆኖ የማረጋገጥ ፣ እና መረጃ የመስጠት ዕድሎችን መፍጠር፤

6) መሻሻል በሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ አሰሪው እንዲያሻሽል /የማሻሻያ ስራው እንዲፈቅድ/ ድጋፍ ማድረግ፤

7) የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች አጠቃላይ የኮንስትራክሽን ሕጎች፣ደንቦች፤ መመሪያዎችና ስታንዳርዶች ተከትለው እየተሰሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ናቸው።

## 5. የፕሮጀክት ኦዲት የኦዲተር ስነምግባር መርሆዎች

ኦዲተሩ የፕሮጀክት ኦዲት ስራውን በሚፈፅምበት ግዜ የሚከተሉት የስነ-ምግባር መርሆዎች ተግባራዊ ማድረግ ይገባዋል፡-

1. በሁሉም የስራና ሙያዊ ግንኙነቶቹ ቀና አመለካከት ያለው እና ታማኝ ሆኖ መገኘት ይኖርበታል፤
2. ሙያዊ ስራውን በሚፈፅምበት ወቅት በሀላፊነት ስሜትና በትጋት እንዲሁም ቴክኒካዊና ሙያዊ ስታንዳርዶች ተከትሎ መሆኑን ማረጋገጥ፤
3. ሙያዊ አስተያየቱን ሲሰጥ ከአድልዎ፣ ከጥቅም ግጭት እና ከሌሎች ወገኖች አላስፈላጊ ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መልኩ መሆን ይኖርበታል፤
4. የተለየ የሕግ ወይም የሙያ ግዴታ የሚያስገድደው ካልሆነ በስተቀር ፤ከሚመለከተው አካል ተገቢ መመሪያ ሳይሰጠው በስራው ምክንያት ያገኘው መረጃ ለሌላ ሶስተኛ ወገን አሳልፎ መስጠት ወይም በማንኛውም ሌላ መንገድ እንዲታወቅ ያለማድረግ፤
5. ማንኛውንም ስራ ሲያከናውን አግባብነት ካላቸው የኮንስትራክሽን ህጎች፤ ደንቦች፤ መመሪያዎች እንዲሁም ከሙያ ስነምግባር ጋር የማይቃረን መሆኑን ማረጋገት፤

# ክፍል ሁለት

## የፕሮጀክት ኦዲት አፈፃፀም ክፍሎችና ደረጃዎች

### 6. የፕሮጀክት ኦዲት የሚፈጸምባቸው የክዋኔ ኦዲት ክፍሎች

የፕሮጀክት ኦዲት ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የክዋኔ ኦዲት የአፈጻጸም ስልቶች ይፈጸማል።

1. በተመረጡ ፕሮጀክቶች ሂደቶች ላይ ተመስርተው የሚከናወን ምርመራ፤ ይህ ምርመራ የሚከናወነው የፕሮጀክቶች መዘግየት ሲኖር፤ ያላግባብ የወጣ ወጪ ሲኖር፤ ጥራት በሌለው ሁኔታ ስራዎች ሲከናወኑ፤ ውጤታማ ያለመሆኑን የሚያመላክቱ ሁኔታዎች ወይም ስጋት ሲኖር ነው።
2. ሰፋ ባለ ሁኔታ ተመስርቶ የሚከናወን ምርመራ፡- በጣም አስፈላጊ መሰረታዊና ችግር ፈቺ በሆኑ ብዙሃኑን ተጠቃሚ የሚያደርጉና ትልቅ በጀት በሚያዝላቸው ፕሮጀክቶች ላይ ትኩረት የሚያደርግ
3. የአስተዳደር ስራ ደረጃዎችን በመፈተሽ የሚደረግ ዋና ምርመራ፡- የተለመደውን አካሄድ ወይም ቅደም ተከተል ላይ ተመስርቶ መመርያን በመከተል የሚከናወን ሆኖ ኦዲቱ እንደባለሙያ፤ አማካሪ፤ስራ ተቋራጭ ፤የግንባታ የመጠቀሚያ ...ወዘተ የመሳሰሉት የፍቃድ አሰጣጥ የኦዲት አካባቢዎች ላይ በመምረጥ አጠቃላይ ድርጅቱን ወይም ስራውን የሚመሩ ወይም የሚፈጽሙ የስራ ክፍል ኦዲት ያደርጋል።
4. ድንገተኛ የሆነና ያልታቀደ ምርመራ ፡- በተከሰተው ችግር ወይም የተፈጸሙ ተግባራት ምክንያት ጥቆማዎች ሲኖሩ ወይም ኦዲት ይደረግልን የሚል ጥያቄ ሲቀርብ የሚደረግ ምርመራ ነው።

### 7. የፕሮጀክት ኦዲት ዓይነቶች

የኮንስትራክሽን ኦዲት ከዚህ ቀጥሎ በተመለከቱት ዋና ዋና ዓይነቶች ይፈፀማል፡-

1) የፋይናንስ መረጃዎችን ትክክለኛነትና አስተማማኝነት የሚያረጋግጥ የፋይናንስ ኦዲት፣
2) ስራዎች ሕግና ደንብን በጠበቀ አግባብ መፈፀማቸውን የሚያረጋግጥ የአፈፃፀም ኦዲት፣
3) ለፕሮጀክቱ የወጣው ወጪ ወይም ገንዘብ እና የስራው መጠንና ዋጋ /Value For Money/ተመጣጣኝ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ የሚደረግ ኦዲት፣

4) የፕሮጀክት ፕሮፖዛል ፤ዲዛይን፤ የስራ ዝርዝርና የጨረታ ሰነድ እንዲሁም ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሚደረግ ኦዲት
5) ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው በጀት፤ጊዜና ጥራት እንዲሁም ሌሎች መስፈርቶችን አሟልተው ስለመከናወናቸው የሚደረግ ኦዲት
6) በኮንስትራክሽን ዘርፍ የስራ ፍቃድ አውጥተው የተንቀሳቀሱ ያሉ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ላይ በተሰጣቸው የሙያና የስራ ፍቃድ ልክ በትክክል የሰሩ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ የሚደረግ ኦዲት
7) በኮንስትራክሻን ዘርፍ የሚሰጡ የሙያና የስራ ፍቃዶች ህግና ደረጃቸውን አሟልተው የተሰጡ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚደረግ ኦዲት ናቸው

## 8. የኦዲት ስራው አፈፃፀም ወሰን

1) የፕሮጀክት ኦዲት አንድን ፕሮጀክት ከቅድመ ግንባታ ጀምሮ እስከ ፕሮጀክቱ ፍፃሜውና ርክክቡ ድረስ ያለውን ሂደት የማየት ወሰን ይኖረዋል።

## 9. ኦዲት የሚደረጉ ፕሮጀክቶችን ስለመምረጥ

ፕሮጀክቶች በቁጥር በርካታ በመሆናቸውና አንድን ፕሮጀክት ኦዲት ለማድረግ ረጅም ሂደትን ስለሚከተል እነዚህን በሙሉ ኦዲት ማድረግ ስለማይቻል ፕሮጀክቱን መምረጥና ኦዲቱ መወሰን አስፈላጊ ነው። ኦዲት የሚደረጉ ፕሮጀክቶችን ከአጠቃላይ ውስጥ የመምረጥ አላማ ይበልጥ ችግር ያለባቸውን ፕሮጀክቶችና ሂደቶችን ትኩረት ሰጥተን የስጋት አካባቢዎችን በመለየት እንድናይ ያደርገናል። በመሆኑም አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመሰብሰብ የሚከተሉትን የመምረጫ ነጥቦች መሰረት በማድረግ ፕሮጀክቱ ወይም ስራው መመረጥ ይኖርበታል።

1. የባለድርሻ አካል ወይም የህዝቡ ፍላጎት ሲኖር
2. ከፍተኛ የሆነ ኢንቨስትመንት ስጋት ያለበት ፕሮጀክት
3. የፕሮጀክት መጓተት ወይም ለሌላ ጊዜ መተላለፍ ሲኖር
4. የማጭበርበር አዝማሚያዎች በፕሮጀክቱ ላይ ከታየ
5. የተጨማሪ ስራ ወይም የክፍያ ጥያቄ /Claim/ ከነበረበት
6. በሳይት፤በዲዛይን፤ በስፔስፊኬሽን.....ለውጥ ምክንያት ካለና የወጪ መናር ከተስተዋለ
7. የተቋረጠ ፕሮጀክት ሲኖር
8. ከዚህ በፊት የተሰሩ የኦዲት ስራዎች ሆነው ተከታታይ የኦዲት ስራ የሚያስፈልግ ሆኖ ከተገኘ

## 10. ስለ ኦዲት ደረጃዎች

የኦዲት ደረጃዎች ከዚህ እንደሚከተለው የተዘረዘሩት ናቸው

1) ኦዲተሩ ኦዲቱን ሲያከናውን ብቃት፣ ችሎታ፤ አስፈላጊው ነፃነትና ገለልተኝነት እንዲሁም ሙያዊ ጥንቃቄን የሚያካትት አጠቃላይ ደረጃዎች
2) የፕሮጀክቱ አሰሪ ወይም ባለቤት ፍላጎት መረዳትን፣ የኦዲት አቀራረብና ዘዴን፣የኦዲት መስፈርትን፤የኦዲት ማስረጃን በስሩ የሚይዘው የመስክ ሥራ ደረጃ ነው።
3) የኦዲት ሪፖርቱን የሚያቀርብበት አሠራር፤ ቅርፅና ይዘት ምን መሆን እንዳለበት የሚገልፅ የኦዲት ሪፖረት ደረጃ ነው።

# ክፍል ሶስት

## የፕሮጀክት ኦዲት ዋና የስራ ሂደት እንዲሁም የኦዲተሮች ተግባርና ሀላፊነት

የፕሮጀክት ኦዲት ዋና የስራ ሂደት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚካሄዱ የመንግስት እና በህዝብና በመንግስት በጋራ የተሰሩ ፕሮጀክቶችን ክዋኔና ፋይናንሽያል ኦዲት በማድረግና በኦዲት ግኝቶች ላይ የእርምት እርምጃ ስለመወሰዱ በመከታተል የአሰራር ሂደቱ የኮንስትራክሽን ህግን እንዲከተል ማስቻል ሲሆን በሌላ በኩል በኮንስትራክሽን ዘርፍ ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ፍትሃዊና ወቅታዊ የሆነ ምላሽ መስጠት ነው።

11. **የሥራ ሂደቱ ዋና ዋና ተግባራት (አገልግሎቶች)**

- ✓ ክዋኔ ኦዲት /performance Audit / ማከናወን
- ✓ ፋይናንሽያል ኦዲት / Financial Audit / ማከናወን
- ✓ ውጤትን መሰረት ያደረገ የፕሮጀክት ተሳታፊዎችን መለየት
- ✓ በኮንስትራክሽን ዘርፉ የሚስተዋሉ ቅሬታዎችን መፍታት
- ✓ የሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ትክክለኛነትን ማረጋገጥ

12. **የፕሮጀክት ኦዲት ዋና የስራ ሂደት መሪ ተግባርና ኃላፊነት**

የፕሮጀክት ኦዲት መሪ የተሰጠው ኃላፊነት የኦዲት ስራው በሁሉም ባለድርሻ አካላት ተቀባይነት ሊኖረው በሚያስችል አግባብ የተቀረፀውን ፕሮግራም በስራ መተርጎም ሆኖ ዝርዝሩ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

1. የፕሮጀክት ኦዲት ተገቢውን የኮንስትራክሽን ስራ ደረጃዎችና ህጎች መሰረት መከናወናቸውን በማረጋገጥ የኦዲት ስራውን ይመራል፤ ሪፖርት ያቀርባል
2. ለግንባታ የወጣው ወጪና የስራው መጠንና ዋጋ/Value for Money/ ተመጣጣኝ መሆናቸውን የሚገናዘብበት አሰራር ይዘረጋል
3. ፕሮጀክቶች የአዋጭነት ጥናት፤የዲዛይን ስራ፤ የስራ ዝርዝርና የጨረታ ሂደት ላይ ተያያዥ ጉዳዮችን ኦዲት እንዲደረጉ ያደርጋል
4. የግንባታ ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው በጀት፤ ጊዜና ጥራት እንዲሁም ሌሎች መስፈርቶች አሟልተው ስለመከናወናቸው ኦዲት እንዲደረጉ ያደርጋል
5. የፕሮጀክቱ ኦዲቱ ከሂደቱ የሙያ ደረጃና አግባብነት ከሚኖራቸው አጠቃላይ የኦዲት ስነምግባር ደንቦች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ መከናወኑን ያረጋግጣል
6. ስራው ውጤታማ በሆነና ብቃት ባለው መንገድ ማከናወን ያረጋግጣል

7. ኦዲቱ በኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ውስጥ ስጋት ያለባቸውን የስራ አከባቢዎች ለይቶ በማወቅና በመቆጣጠር መልካም አስተዳደርን እንዲሰፍን አስተዋጽኦ ማድረግ
8. አግባብነት ያላቸው ሕጎች ደንቦችና መመርያዎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ
9. የፕሮጀክቱን ኦዲት የሚያከናውነው ስራ ተጨማሪ እሴት የሚፈጥር እና የፕሮጀክቱን አሰራር ሊያሻሽል የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ፤
10. የኦዲት ሪፖርቶችን ለቢሮ ኃላፊ ያቀርባል

## 13. የኦዲተር ተግባርና ኃላፊነት

1. የፕሮጀክት የአዋጭነት ጥናት ኦዲት ያደርጋል
2. ዲዛይኖች ተገቢውን ኮድ፤ ስታንዳርድና ሌሎች መስፈርቶችን አሟልተው ስለመሰራታቸው ኦዲት ያደርጋል
3. ለዲዛይን ስራው በግብዓትነት የዋሉ የላብራቶሪ የአፈር ምርምራ ውጤት ስለመኖሩና ስለትክክለኝነቱ ያረጋግጣል
4. የጨረታ ቴክኒካል መስፈርቶች በሚመለከተው አካል ጸድቆ ለሁሉም ተሳታፊዎች እኩል እድል የሰጡ መሆናቸውን ኦዲት ያደርጋል
5. ዲዛይንና የስራ ዝርዝሩ የተጣጣመ መሆኑን ኦዲት ደርጋል
6. ግንባታዎች በሂደት ላይ እያሉ በተቀመጠው የስራ መርሃ ግብር /Schedule/ መሰረት እንዲሁም በፕሮጀክቱ የተሰማራው የሰው ኃይል፤ ማሽነሪና ተገቢው ግብዓት ተሟልተው ስለመከናወኑ ኦዲት ያደርጋል
7. የተጠናቀቁ ግንባታዎች በተቀመጠላቸው ዲዛይንና ጥራት የተገነቡ መሆኑንና በሳይት ላይ የቀረቡ የግንባታ ግብዓቶች ፍተሻ ያስፈልጋቸዋል ብሎ ካመነ እንዲመረመሩ በማድረግ ኦዲት ያደርጋል
8. ከመሬት በታች የተገነቡ ግንባታዎች አጠራጣሪና ችግር ያለባቸው ናቸው የሚል ጥቆማ ከደረሰው ወይም ግምት ከወሰደ የሚመለከተውን ሃላፊ ይሁንታ በማግኘት ቁፋሮ ተደርጎላቸው ኦዲት ማድረግ ስራ ይሰራል
9. የክፍያ የምስክር ወረቀቶችና የምህንድስና ስፍር ልኬት /Takeoff Sheet/ ሰነዶች የግንባታ ውጤትን መሰረት አድርጎ ስለመፈጸማቸው ኦዲት ያደርጋል
10. የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች በጊዜ፤በተቀመጠላቸው ዲዛይንና በጀት እንዲሁም በታቀደላቸው አገልግሎት እንዲውሉ ሆኖ ስለመጠናቀቃቸው ኦዲት ማድረግ

# ክፍል አራት

## የፕሮጄክት ኦዲት የአሰራር ሂደት

14. **የኦዲት ስራ ከመጀመሩ በፊት** ስለሚከናወኑ ተግባራት

1. ማንኛውም ኦዲተር የኦዲት ስራውን ከመጀመሩ በፊት ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ተግባራት የሚያካትት ዝግጅት ማድረግ ይኖርበታል፤

    ሀ. ለስራው የሚያስፈልግ የሰው ኃይልና እያንዳንዱን ተግባርና ኃላፊነት በዝርዝር የሚያሳይ የኦዲት እቅድ ማዘጋጀት፤

    ለ. ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ በኮንስትራክሽን ፕሮጀክቱ ላይ የተከናወነ የኦዲት ስራ ካለ የመከለስና የማገናዘብ ተግባር ያከናውናል፤

    ሐ. የኦዲት ስራ እቅዱን ለቢሮ ኃላፊ አቅርቦ  ማጸደቅ

    መ. ኦዲት የሚያደረግበትን ጊዜና ሊከናወኑ የታቀዱ ስራዎችን የያዘ የድርጊት መርሃ ግብር ማዘጋጀት፤

    ሠ. አስፈላጊ የሆኑ ማስታወሻዎች፤ዝርዝር ቼክሊስቶች ማዘጋጀት፤

    ረ. ኦዲት ለሚደረገው የስራ ክፍል የኦዲቱ ወሰን አጠቃላይ የፕሮጀክቱን ሂደት ወይም የተወሰነ ደረጃውን የሚያጠቃልል ስለመሆኑ ማሳወቅ፤

    ሰ. በአግባቡ መረጃዎችን ለመያዝ እንዲቻል በቋሚነት የሚሞሉ ሰነዶችንና ቅጾችን ማዘጋጀት፤

    ሸ. ለዝግጅት እንዲረዳው ለኦዲት ስራው አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች እና የሰው ኃይል ዝርዝር ቅድመ ሁኔታዎችን የያዘና ኦዲት እንደሚደረግ የሚገልጽ ደብዳቤ ለኦዲት ተደራጊው መስጠት፤

2. ኦዲተሩ የኦዲት ስራውን ከመጀመሩ በፊት ኦዲት ተደራጊውን በሚያገኝበት ወቅት የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርበታል፤

    ሀ. የኦዲት ስራው የኦዲት ተደራጊው ግዴታውን በአግባቡ እንዳይወጣና የስራ ክፍሉን መልካም የሆነ የስራ እንቅስቃሴ የሚገድብ እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ፤

    ለ. የኦዲቱ ዓላማ አጠቃላይ የፕሮጀክቱን ስራና እንቅስቃሴ ህጉንና የአሰራር ሂደቱን በተከተለ መልኩ መሆኑን ለማረጋገጥና ለመርዳት እንደሆነ ማስገንዘብ

    ሐ. የኦዲት ተግባር ስህተትን ለመፈለግ ወይም ለመቅጣት እንደልሆነና በኦዲቱ ወቅት  ከሚገኙት ስህተቶች ለመማር እንደሆነ ማስገንዘብ፤

## 15. በኦዲት ስራ ወቅት ስለሚከናወኑ ተግባራት

ኦዲተሩ በጸደቀው ፕሮግራም መሰረት የኦዲት ስራውን በሚሰራበት ወቅት የሚከተሉትን ተግባራት ማከናወን አለበት፤

1) ከኦዲት ተደራጊውና በኦዲቱ ከሚሳተፉ ጋር የመክፈቻ ውይይት ማድረግ፤የኦዲቱን ወሰን፤የሚቆይበትን ጊዜ፤አስፈላጊ ዶክመንቶች፤ሪፖርት ስለሚደረግበት መንገድ እና በሌሎችም አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ገለጻ መስጠት፤
2) አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ህጋዊነት ማጣራት፤
3) የፕሮጀክቱን ክዋኔና ፋናንሻል ሂደት ሰነዶችን በመመርመር ኦዲት ማድረግ ግንቶችን መዝግቦ መያዝ
4) ፕሮጀክቱ የሚገኝበትን ሳይት በመጎብኘት ስራው ስለሚገኝበት ደረጃ፤ስለግንባታው ማቴሪያል ሁኔታ ማብራሪያ ማግኘት፤
5) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለኦዲት ተደራጊው በየጊዜው ስለኦዲቱ በቃል ወይም በጽሁፍ ሪፖርት መግለጫ መስጠት፤

## 16. በኦዲት ስራ ማጠናቀቂያ ወቅት ስለሚከናወኑ ተግባራት

የኦዲት ስራው በሚጠናቀቅበት ወቅት ኦዲተሩ ከኦዲት ተደራጊው ጋር አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ሳይቱ በሚገኝበት ቦታና በኦዲት ተደራጊው ቢሮ በመገኘት የመጨረሻ የመዝጊያ ስብሰባ ያደርጋል፤ አስቀድሞ ግን የሚከተሉት መከናወናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡-

1) የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቱ ኦዲት ምርመራው ውጤት ከኦዲቱ ዓላማ እና ወሰን አንጻር መመዘኑን ማረጋገጥ አለበት፤
2) የውይይት ውጤት በሰነድ መያዙን፤
3) በኦዲቱ ግኝት ላይ ወይም በኦዲተሩ እይታና በተሰጠው መደምደሚያ ላይ ኦዲት ተደራጊው ያልተስማማባቸው ነጥቦች እንዲሁም የሚያነሳቸው ደጋፊ የሆኑ ምክንያቶችን ለይቶ መያዝ፤

## ክፍል አምስት

## የፕሮጀክት ኦዲት የአፈጻጸም ሂደት

### 17. የቅድመ ግንባታ ኦዲት

17.1 በዲዛይን ሂደት መታየት ያለባቸው ጉዳዮች

1. የፕሮጀክት ዲዛይን ሃሳብና የአዋጭነት የሚቀርብላቸው ግንባታዎች በልዩ ጥናት ስለመዘጋጀቱና መዘጋጀት ባለበት ደረጃ ስለመሆኑ ማረጋገጥና የሚከተሉትን የያዘ ሰነድ መሆን አለበት
   - ሀ. ፕሮጀክቱ የህብረተሰቡን ተጨባጭ ችግር መነሻ ያደረገ መሆኑን
   - ለ. የፕሮጀክቱ መሰራት የታየውን ችግር ለመፍታት የተሻለ አማራጭ መሆኑን
   - ሐ. ከሚወጣው ወጪ አኳያ የተሻለ ጥቅም የሚስገኝ መሆኑን
   - መ. ፕሮጀክቱ የታቀደለትን አላማ ሊያሳካ ስለመቻሉ
   - ሠ. ለህብረተሰቡ እና የአካባቢው ነዋሪዎች የተሻለ የስራ እድል ስለመፈጠሩ
2. የፕሮጀክት ቦታ ከይዞታ ነጻ መሆኑን የሚያሳይ ካርታ ስለመኖሩ ማረጋገጥ
3. ፕሮጀክቱ በጀት የተያዘለት ስለመሆኑ የሚያሳይ መረጃ መኖሩን ማረጋገጥ
4. የአፈር ምርምር መደረጉን የሚሳይ ሰነድ ስለመኖሩ ማረጋገጥ
5. ዲዛይን መዘጋጀትቱን፤ የተዘጋጀው የዲዛይን ደረጃ ጠብቆ መዘጋጀቱንና በሚመለከተው አካል መጽደቁን ማረጋገጥ
   - ሀ. ዲዛይኑ አግባብነት ያላቸውን ኮዶች፤ ስታንዳርዶችና ሌሎች መስፈርቶችን መሰረት በማድረግየመጀመርያውን የአርክቴክቸራል ፤ስትራክቸራል፤ ኤሌክትሪካል፤ ሳኒቴሪና የሜካኒካል ዲዛይኖች ተካተው መዘጋጀታቸውና የመጀመሪያ ግምገማ መካሄዱን ኦዲት ያደርጋል
   - ለ. የተሰራው ዲዛይን የአፈር ምርመራ ውጤትን መሰረት ያደረገ ስለመሆኑ
   - ሐ. በዲዛይን ግምገማ ወቅት የተገኙ ግብአቶችን ያካተተ የመጨረሻ ዲዛይን ስለመዘጋጀቱና በመመርያው መሰረት በሚመለከተው አካል መጽደቁን ኦዲት ያደርጋል

6. ዲዛይን የተሰራለት ፕሮጀክት የተሟላ ዲዛይን መሆኑና የተሰራው የስራ ዝርዝር /BOQ/ ከዲዛይኑ ጋር ማመሳከርና ማረጋገጥ

17.2 **የጨረታ ሂደትን በተመለከተ**

1. ስታንዳርዱን የጠበቀ የጨረታ ሰነድ መዘጋጀቱንና በሚመለከተው አካል የጸደቀ መሆኑን ማረጋገጥ
2. ጨረታው አየር ላይ መዋሉን ወይም አነስተኛ ከሆነ ሰሌዳ ላይ መለጠፉን ማረጋገጥ
3. የጨረታው ሰነድ ሽያጭ በፋይናንስ በኩል መካሂዱን ማረጋገጥ
4. በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት የጨረታው ሰነድ መከፈቱን ማረገገጥ
5. ህጋዊ የሆኑ የጨረታ ማስከበርያ የዋስትና ሰነዶች መያዛቸውን ማረጋገጥ
6. ተጫራቾች በተቀመጠው ቴክኒካል መስፈርት መሰረት በትክክል መመዘናቸውን ማረጋገጥ
7. የፋይናንሻል ግምገማው በትክክል መካሄዱን ማረጋገጥ

17.3 **በውል ሰነድ ዝግጅት ጌዜ**

በጨረታው ውጤት መሰረት ስታንዳርዱን የጠበቀ የውል ሰነድ መዘጋጀቱን ለማረጋገጥ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መመልከት ያስፈልጋል፡

1) በጨረታው ሰነድ ላይ በተተነተነው መሰረት የውድድር ሂደቱን መከናወኑን ማረጋገጥ
2) በጨረታው ሰነድ በተተነተነ መንገድ አሸናፊው የስራ ተቃራጭ የተለየበትን መንገድ እና በሚመለከተው ሀላፊ መጽደቁን
3) አሸናፊው ተወዳዳሪ በማስታወቅያ ሰሌዳ ላይ መለጠፉን ወይም በደብዳቤ መገለጹ
4) ከአሸነፊው ስራ ተቃራጭ ጋር ውል መፈራረሙን
5) ህጋዊ የሆኑ የውል ማስከበርያ የዋስትና ሰነዶች መያያዛቸውን

## 18. በግንባታ ሂደት

በግንባታ ወቅት በሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት የሚደረግ ኦዲት

የፕሮጀክቱ ግንባታ አይነቶች በተቀመጠላቸው ግዜ መጠናቀቃቸውን ኦዲት ስለማከናወን

1) ሰራዉ ከመጀመሩ በፊት በተገቢዉ የስራ የጊዜ የማቴርያልና ዝርዝር (Work,Time and Material & Human Resource Break down Structure) የያዘ የግዜ ሰሌዳ መዘጋጀቱን ማረጋገጥ
2) በቀረበው የስራ ዝርዝር መሰረት ስራው የተከናወነ መሆኑን ማረጋገጥ

3) የክፍያ ሰነዶች በአማካሪው በኩል ጸድቆ ላሰሪው መ/ቤቶች ከቀረበ ቦሃላ ባለው የፋይናንስ ህግ መሰረት ክፍያውን መፈጸሙን ማረጋገጥ
4) የወጣው ወጪና የተከናወነው የግንባታ ስራ ተመጣጣኝ ስለመሆኑ ማረጋገጥ
5) ተጨማሪ ስራ እና የስራ ለውጥ ካለ የስራ ትእዛዝ ካሰሪው መ/ቤት ጥያቄ ቀርቦ በአማካሪው ታምኖበትና በሚመለከተው አካል መጽደቁን ማረጋገጥ
6) ለግንባታ የሚውሉ በአስገዳጅነት የተጠቀሱ ግብዓቶች ህጋዊ በሆነ ተቋም ፍተሻ ተደርጎባቸው ያለፉና ማረጋገጫ ሰነድ ያላቸው ማረጋገጥ
7) የግዜ ይራዘምልኝ ጥያቂ ካለ ተገቢነቱን ማየትና ማረጋገጥ

## 19. ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀ በኋላ /ድሕረ-ግንባታ/ የሚፈፀም ኦዲት

አንድ የተጠናቀቀ የግንባታ ስራ የሚከተሉት ጉዳዮች መረጋገጥ አለባቸው

1) የተወሰደው የቅድሚ ክፍያ ብር ተከፍሎ ማለቁን ማየት
2) የመያዣ ገንዘብ /Retention/ ተቀንሶ የተያዘ መሆኑን አግባብ ባለው የፋይናንስ ህግ መሰረት ተመላሽ ተደርጎም ከሆነ ኦዲት ማድረግ
3) በውሉ የተመለከተውን ወጪ ከተደረገው ጠቅላላ ሂሳብና የተጠናቀቀውን ስራ ከሚያሳየው መረጃ ጋር በማወዳደር የታውን ልዩነት መጠን ማየትና ማጣራት
4) የግንባታ ስራው በውሉ መሰረት በባለሙያ ተረጋግጦ መጠናቀቁ እና ርክብክብ የተደረገበት ሰነድ ማረጋገጥ
5) ስራዎቹ በየደረጃው ክትትል የተደረገባቸው ለመሆኑ የባለሞያ መከታተያ ሰነድ ማረጋገጥ
6) በተፈቀደው ፕላን መሠረት መጠናቀቁን የሚገልፅ የርክክብ ሠነድ መቅረቡን ማረገገጥ።
7) የተያዙ የዋስትና ሰነዶች አግባብ ባለው የፋይናንስና የውል ህጎች መሰረት ተፈጻሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ
8) ከፊል ርክክብ፤ የመጀመርያ ርክክብ ወይም የመጨረሻ ርክክብ ባለው የአሰራር መመርያ መሰረት ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ

## 20. የሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ትክክለኛነትን ማረጋገጥ

1) የኦደት ቡድን የሚመራበት ቢጋር በማዘጋጀት ማስገምገምና ማጸደቅ
2) ከኦዲት ቡድን ጋር ስለ ስራው የጋራ ማድረግና ስራ መከፋፈል
3) ከኦዲት ተደራጊው አካል ጋር መግቢያ ውይይት ማድረግ

4) ቢያንስ 25% ሳምፕል በመውሰድ ሰነዶችን ደረጃ በደረጃ መረከብ
5) ሰነዶችን የመፈተሽ ስራ መስራት
6) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመስክ ምልከታ ማድረግ
7) ሪፖርት ማዘጋጀት

# ክፍል ስድስት

## 21. ስለኦዲት ሪፖርት መዝጊያና ክትትል

### 21.1 ስለፕሮጀክት ኦዲት ሪፖርት አቀራረብ

ማንኛውም ኦዲተር በኦዲት አቀራረብ ወቅት ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን ሂደቶች መከተል ይኖርበታል፤

1) በኦዲት የተገኙ ግኝቶችን ለማጠናቀር የኦዲት ሪፖርት መዝጊያ ላይ ከሚመለከተው የኦዲት ተደራጊ አካል ጋር ውይይት ማድረግ
2) የኦዲት ሪፖርት ከመጽደቁ በፊት አጠር ባለ መልኩ ዝርዝር ሁኔታዎችን ያካተተ የመጨረሻ ጥቅል ኦዲት ሪፖርት በማዘጋጀት ለኦዲት የስራ ክፍል ማቅረብ አለበት
3) የምርመራ ግኝት ሪፖርት ጠቃሚ፤ጥራቱንና ጊዜውን የጠበቀ፤ አግባብነት ያለውና አስተማማኝ መረጃ ያላቸው ለሌሎች አስተማሪና አስጠንቃቂ ሆኖ መቅረብ አለበት፤
4) በመጀመርያ ሪፖርት ላይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በተደረገው ግምገማ የተገኘው ግብዓት ተካቶ ለሚመለከተው አካል መላክ፤

### 21.2 በኦዲት ሪፖርቱ ላይ ስለሚደረግ ክትትል

1) የኦዲት ስራ ክፍሉ በኦዲት ሪፖርቱ መሰረት የተሰጡ የማሻሻያ ሀሳቦችን ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ የክትትል ስርዓት መዘርጋት አለበት ፤
2) በተዘረጋው የክትትል ስርዓት መሰረት ክትትል መደረጉንና እርምጃ መወሰዱን የተወሰደው እርምጃም የተፈለገውን ውጤት ማስገኘት መቻሉን መገምገም አለበት፤

# ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 22. የኦዲት ተደራጊ ግዴታዎች

22.1 የፕሮጀክት ኦዲት ስራው በሚከናወንበት ጊዜ፡-

1) ማንኛውም በኮንስትራክሽን ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ወይም ድርጅት ኦዲት የማስደረግ እንዲሁም በቃልና በፅሑፍ ለሚቀርብለት ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ የመስጠት ግዴታ አለበት፤
2) ማንኛውም የፕሮጀክት አሰሪ ወይም ባለቤት ከኦዲት ስራው ተያያዥነት ያላቸው በስሩ የሚገኙ ሰነዶችና ሰራተኞች አስቀድሞ ዝግጁ ከማድረግ ጀምሮ ሌሎች በኦዲተሮች የሚፈለጉ ለስራው አፈፃፀም ጠቃሚ የሆኑ ተግባራት የመፈፀም ግዴታ አለበት።
3) ማንኛውም አማካሪ ለፕሮጀክት ኦዲት ስራው አፈፃፀም የሚጠበቅበትን ከመፈጸም አኳያ ከዚህ በላይ ለፕሮጀክት ባለቤትና ስራ ተቋራጭ የተደነገጉ ግዴታዎች አሉበት።

### 23. የመተባበር ግዴታ

አግባብነት ያላቸው መንግስታዊም ሆነ የግል ተቋማት እንዲሁም የሚመለከታቸው ሰዎች ይህን መመሪያ ከማስፈፀም አኳያ የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

### 24. መመሪያውን ማስፈፀሚያ ማንዋሎች ስለማውጣት

የፕሮጀክት ኦዲት የስራ ሂደት መመሪያውን ለማስተግበር የሚረዱ ዝረዝር የአሰራር ስርዓቶችና ማንዋሎች ሊያወጣ ይችላል።

### 25. መመሪያውን ስለማሻሻል

ቢሮው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ያሻሽላል።

### 26. መመሪያው ሚፀናበት ግዜ

ይህ መመሪያ በቢሮ ሃላፊው ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

መጋቢት1/2010 ዓ.ም

ዮናስ አያሌው /ኢንጂነር/

የአዲስ አበባ ኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊ